# ውሎን/ኮንትራት እንዴት ያነባሉ

# ተከራዮች፡ መብቶቻችሁን አወቁ!

## ውሌን ለምን አነባለሁ?

የቤት **ኪራይ** ስንት እንደሚከሉ ከማሳወቅ ጎን ለጎን ውሎ አፓርታማ ከመከራየቶ **በፊት** ማወቅ የሚኖርብዎት ብዙ **ጠቃሚ መረጃዎችን** ያካትታል። ውሎ በርስዎ እና በአከራዮ መሃከል አሳሪ ኮንትራክት ነው፤ ከፈረሙት በኋላ **መቀየር አይችሉም** ስለዚህ ከመፈረሞ **በፊት በወስጡ ባለ ነገር ሁሉ መስማማትዎን ለራስዎ ያረጋግጡ።**

**ውሎ ውስጥ ባለ ማንኛውም ነገር ካልተስማሙ አይፈርሙት ።**

## ውሌን ሳነብ ምን ማጤን አለብኝ?

ስምምነቱ እርስዎ እና አከራዮ የምትስማሙበትን **ሁሉንም** ነገር መጥቀስ አለበት። **ትክክል መሆኑን አረጋግጡ** ፤ ፍርድ ቤት መሄድ ካለብዎ፤ ስምምነቱ እርስዎ እና አከራዮ ወደ ቤቱ ሲገቡ በነበረበት ወቅት የምትስማሙበትን ነገር **ያረጋግጣል**። ውሎን ሲያነቡ እነዚህን ነገሮች ልብ ይበሉ፡

| | |
|---|---|
| የቤት **ኪራይ** እና **ሲኪውሪቲ ዲፖሲት** ምን ያህል እንደሚሆን | ከግዜዎ **ቀድመው ከወጡ** መክፈል እንዳለብዎ ወይም እንደሌለብዎ |
| አከራዮ እርስዎን ወደ **ፍርድ ቤት** ከመውሰዱ በፊት **መቼ** ማሳወቅ እንዳለበት | **ማን እስከ መቼ** እዛ ቤት መኖር እንደሚችል |
| **የጋዝ ፣ መብራት እና ውሃ** ክፍያን **ማን እንደሚፈጽም** | **የቤት እንስሳት** ማሳደግ ይቻል አይቻል |
| **ማንኛውንም ጥገና እርስዎ ማድረግ** እንዳለብዎ ወይም እንደሌለብዎ | **ለቆሻሻ እና የጊቢ ስራ** ሃላፊነት ይኖርብዎ አይኖርብዎ |
| **አከራዩ ከከሰሰዎ** ምን ያህል **መክፈል እንዳለብዎ** | ሌላ ምንኛውም **መመሪያ** ቤቱ ውስጥ ለመኖር |

**ውሎን ከሰበሩ አከራዮ ሊያስወጦት ይችላል።**
**አከራዮ ስምምነቱን ከሰበረ የማስወጣት መብት ጋር በመደወል ያማክሩ።**

AMHARIC - Reading Your Lease

LEGAL AID SOCIETY (833) 837-HOME
NASHVILLE HISPANIC BAR ASSOCIATION (615) 701-7957
AMAC American Muslim Advisory Council (615) 988-6460
NASHVILLE CONFLICT RESOLUTION CENTER
ROOFTOP NASHVILLE

ይህ መረጃ ለዴቪድሰን ካውንቲ ብቻ ነው። እዚህ የቀረበው መረጃ የህግ ምክር አይደለም ወይም የህግ ምክር ለመመስጠት የታሰበ አይደለም። የሕግ ችግር ካጋጠመዎት፣ እባክዎን ለግል ጠበቃዎ ይደውሉ ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የመካከለኛው ቴነሲ የሕግ ድጋፍ ማህበር እና የኩምበርላንድን ቢሮ በ1-800-238-1443 ይደውሉ ወይም የናሽቪል ሂስፓኒክ ባር ማህበር በ1-615-701-7957 ይደውሉ። 5/24 ተሻሽሏል።

# ውሎን/ኮንትራት እንዴት ያነባሉ

# ተከራዮች ፡ መብቶቻችሁን እወቁ!

## ውሌ ወስጥ ያለ አንድ ነገር ህገወጥ ቢሆንስ?

ውሎ በውስጡ “**የተከለከለ**” ወይም “**የማይታሰብ**” አንቀጽ ሊኖረው ይችላል። በስምምነቱ ውስጥ አንድ ነገር ሀገወጥ ከመሰለዎ **የማስወጣት መብት ጋር በመደወል ያማክሩ**። የተለመደ ህገወጥ የውል አንቀጽ ምሳሌ:-

**አከራዩ ከጥፋት “ነጻ መሆንን” ያሰፍራሉ**። ይህ ማለት አከራዩ መቼም ቢሆን ጥፋተኛ እንደማይሆኑ ወይም በርስዎ ሊከሰሱ እንደማይችሉ ሊያስማማዎት ይሞክራሉ ፤ ምንም እንኳን ቢሳሳቱም። ለምሳሌ ፣ አከራዮ ህግን ቢጥሱ እና እርስዎን ቢጎዳዎት አከራዮን መክሰስ እዳይችሉ መብቱን ይወስዱብዎታል። **ይሄ ህገወጥ ነው**።

አከራዮ ህገወጥ የሆነ አንቀጽ ቢያስገቡ እና እርስዎ ቢፈርሙት ፍርድ ቤቱ አንቀጹ **አያስፈጽምም**። ነገር ግን ሙሉ **ስምምነቱን አያሰርዝም**። የተቀሩትን ሌሎች ህጎች መከተል አለብዎ።

## ውሌ እየተገባደደ ነው ምን ላድርግ?



መውጣት ከፈለጉ ወይም ሌላ ውል መፈረም ከፈለጉ አብዛኛውን ግዜ **ለአከራዩ ቀደም ብለው ማሳወቅ** አለብዎ። አብዛኞቹ ውሎች በውስጣቸው የመመሪያ አቅጣጫዎችን ይይዛሉ። ለመዘጋጀት:-

1. **የውል ግዜ አጋማሽ ላይ ስምምነቱን ደግመው ያንብቡት** ። ለምሳሌ የውል ግዜው 1 ዓመት ከሆነ ቤት ውስጥ ከገቡ ከ 6 ወር በኋላ ደግመው ያንብቡት። ስለ ውል ማደስ በተመለከተ በተለይም “**አውቶማቲክ ማደስ**” አንቀጽ ካለ!
2. ለአከራይዎ ውሎን ስለማደስ ወይም አለማሳደስ አስቀድመው **ማሳወቅ** እንዳለብዎ ያጣሩ። አብዛኛውን ግዜ አከራዮች ከተከራዩ ውልን ስለማደስውይም ስለማገባደድ የ30 ፣ 60 ወይም 90 **ቀን ማስታወሻን** ይፈልጋሉ። መመሪያዎችን ይከተሉ። ማስታወሻዎቿትን **በጽሁፍ** ያስገቡ እናም **ቅጂ ያስቀሩ**!

## መቼ ነው ውሌን መስበር የምችለው እናም ቀድሜ ከቤቱ መውጣት የምችለው?

ያለቅጣት ውሎን ማቋረጥ የሚችሉባቸው ልዩ ሁኔታዎች አሉ። ለምሳሌ :- **የቤትውስጥ ጥቃትን** እያስተናገዱ ከሆነ፣ አፓርታማዎ **በእሳት ፣ በጎርፍ ወይም በአደጋ** ከተጎዳ ወይም አከራዮ **ጥገናዎችን ለማድረግ ፍቃደኛ ካልሆነ**፣ ከውሎ በቀላሉ ሰብረው መውጣት ይችላሉ።

ውሎትን ከልዩ ሁኔታዎች ውጪ **በሌላ ማንኛውም ምክንያት** ካቋረጡ ከቤቱ ከወጡ በኋላ **የቅጣት ክፍያ** ወይም **የተጨማሪ ወራት ኪራይ** መክፈል ሊጠበቅብዎ ይችላል።

**ውሎን ለመስበር እያሰቡ ከሆነ**
**የማስወጣት መብት ጋር በመደወል ያማክሩ።**

AMHARIC - Reading Your Lease

LEGAL AID SOCIETY (833) 837-HOME

NHBA (615) 701-7957

AMAC American Muslim Advisory Council (615) 988-6460

NASHVILLE CONFLICT RESOLUTION CENTER

ROOFTOP NASHVILLE

ይህ መረጃ ለዴቪድሰን ካውንቲ ብቻ ነው። እዚህ የቀረበው መረጃ የህግ ምክር አይደለም ወይም የህግ ምክር ለመመስጠት የታሰበ አይደለም። የሕግ ችግር ካጋጠመዎት፣ እባክዎን ለግል ጠበቃዎ ይደውሉ ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የመካከለኛው ቴነሲ የሕግ ድጋፍ ማህበር እና የኩምበርላንድን ቢሮ በ1-800-238-1443 ይደውሉ ወይም የናሽቪል ሂስፓኒክ ባር ማህበር በ1-615-701-7957 ይደውሉ። 5/24 ተሻሽሏል።